# ፕሮፌሰር ሆይ፣ ምናለበት በዚህ ዕድሜዎ ባይቀላምዱ?!

**ሸረፋ ከድር**

ksherefa@yahoo.com

እናንተዬ!...ለካስ የሀገሬ አርሶ አደር "ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም" የሚለው ያለ ያለ ምክንያት አይደለም– አንዳች ሃቅ በውስጡ ኖሮት እንጂ። ታዲያ ወትሮም ቢሆን አንድን ጉዳይ እንዳመጣለት በዘፈቀደ የማይናገረውን ይህን የወንዜን ሰው ይትብሃል በሚገባ ያረጋገጥኩት ሰሞኑን ነው ብል ቅር የምትሰኙብኝ አይመስለኝም። እርግጥ ለብሂሉ 'አርፍድሃል' የሚለኝ ካለ ለመቀበል ዝግጁ ነኝ፡፡ ለማንኛውም እስቲ ምን አጋጥሞኝ ይህንን ልላችሁ እንደቻልኩ ላውጋችሁ፡፡...

...አንድ የካፌቴሪያ በረንዳ ላይ ተቀምጬ "ፋክት" በሚል ስያሜው የሚታወቀውንና ጋዜጠኛ ያልሆኑ፣ ነገር ግን ጋዜጠኛ መሳይ የፅልመት ተንታኞች ተሰባስበው ሀገራችን ነገ የምትበታተን ያህል መፅሔት እያነበብኩ ነበር— ቅፅ 2 ቁጥር 7፣ የነሐሴ 04 ቀን 2005 ዓ.ም ዕትሙን፡፡ በፊት ሽፋን ገፁ ላይ ከሰፈሩ ጉዳዮች ጀምሬ ማውጫውን፣ የአቶ ተመስገን ደሳለኝ የጥነቆላ ዲስኩርንና ሌሎች ውግዘቶችን፣ ስድቦችንና የአመፅ ጥሪዎችን አለፍ አለፍ እያልኩ ገፅ በገፅ ተመለከትኳቸው። ገፅ አራት ላይ ስደርስ ግን አንድ ነገር ያዝ አደረገኝ፡፡ የአምድ ስም በሌለው በዚህ ገፅ ላይ ከኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት ጀምሮ "እኔ ነኝ ትክክል" በማለት የሚታወቁት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ለሶስተኛ ጊዜ "የስላሴ እርግማን (3) አደህይቶ ማድከም" በሚል ርዕስ፤ ከንጉሱ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ እንደ ተውሳክ የተጣባቸውን የ"ከእኔ ወዲያ ላሳር" ትምክህታቸውን ተመለከትኩ። የትምክህታቸው ቋጠሮ ደግሞ የኢፌዴሪ መንግስት የከተማውን ህዝብ የቤት ባለቤት በማድረግ የኑሮ ሁኔታውን ለማሻሻል ያቀደውን የኮንደሚኒየም ቤት ግንባታን የሚያወግዝ፣ ህዝቡን ስግብግብ እያለ የሚሰድብ ብሎም የተሳሳተ የሂሳብ ስሌት በመስራት የህዝቡን የልማት ተነሳሽነት ለማምከን የሚጥር ነው። እናም ፕሮፌሰሩ በዚህ ዕድሜያቸው ስለ ኮንደምኒየም ቤቶች ግንባታ የቀላመዱት ጉዳይ፤ ፈፅሞ ከእውነት የራቀ፣ አላዋቂነትና ግልብነት የሚታይበት እንዲሁም በጭፍን ተቃውሞአዊ ጥላቻ የታፈነ ምልከታን የያዘ በመሆኑ በሰውዬው ቦታ ሆኜ በማፈር ብዕሬን እንዳነሳ አድርጎኛል።...

'ሁሉንም ነገር ከእኔ ውጭ የሚያውቅ የለም' በማለት ይታወቃሉ የሚባሉት፣ ዳሩ ግን ምልከታቸው ምሁራዊ ሳይሆን ፖለቲካዊ መሆኑ የሚነገርላቸው ፕሮፌሰር መስፍን፤ ለፅልመት ፅሑፋቸው መግቢያ ማዳመቂያ ያደረጉት አንድ ደቡብ አፍሪካዊ ግለሰብን በገፀ-ባህሪነት በመፍጠር ነው—ለዚያውም ግለሰቡ ላይ "...ለወትሮው ብዙ የምክር ዋጋ የሚያስከፍል ቢሆንም ለመንግስትህ

እንዳትናገርና የዚሁ ዓይነት ስራ በደቡብ አፍሪካ እንዳይጀመር ቃል ግባልኝ።...” እያሉ በመታበይ።... “አይ ምክር! ድንቄም መካሪ!” አሉ የመንደራችን ቀልደኛ እማማ ኩሪ።...እንግዲህ ይታያችሁ!...ፊደላዊው ፕሮፌሰር መካከለኛ ገቢ ላይ ያለችውና በማህበራዊ-ኢኮኖሚ አስተሳሰቧ ከአፍሪካ ቀዳሚውን ቦታ እየያዘች ያለችው ደቡብ አፍሪካ ሃሳባቸውን እንዳትኮረጅ ሰጉ ማለት ነው። እንዴትም ተቀልዶ ጃል?!...

እኔ ግን ፕሮፌሰሩ የታበዩበትን “መካሪነት” በፅሑፋቸው ሲግሩን ትዝ ያለኝ ነገር ቢኖር፣ ሰውዬው በአንድ ወቅት በሀገራችን ለነበረው መንግስት የለገሱትና ትክክለኛ ማንነታቸውን የሚገልፀው ፀረ-ህዝብ ምክራቸው ነው። ነገሩም እንዲህ ነበር።...ምናልባትም ጊዜው ከዛሬ 33 እና 34 ዓመት በፊት ይሆናል–በአምባገነኑ የደርግ ስርዓት ወቅት። ታዲያ በዚያን ወቅት አምባገነኑ መንግሰቱ ኃይለማሪያም የሀገራችንን ዜጎች በኢህአፓ ስም ሲጨፈጭፉ አጠገባቸው ከሚገኙት አማካሪዎች ለአንዱ መራር ጥያቄ ያቀርባሉ። እኚህ ሰው በአንድ ወቅት የአንድነት ፓርቲ አባል ሆነው መሃል ላይ በስልጣን ጥማታቸው ምክንያት በአጠና ከተገለጡና በድንጋይ ከተዋገሩ በኋላ ፖርቲውን መልቀቃቸው የሚነገርላቸው የዛሬው የወረቀት ላይ ነፍጥ አርበኛው ፕሮፌሰር መስፍን ናቸው።

እናም የሰው በላው ስርዓት መሪ ፕሮፌሰሩን “ኢህአፖዎች እያስቸገሩን ነው። ምን እናድርጋቸው?” ሲሉ ይጠይቋቸዋል፡፡ የዛሬው ዴሞክራት መሳይ ኘሮፌሰርም ወትሮም በፀረ-ህዝብነት የተሰለፉ በመሆናቸው ቀልጠፍ ይሉና “ታዲያ እኛን ምን አድርጉ ትሉናላችሁ፣ መሳሪያው ያለው እናንተው ጋ አይደለም ወይ?” የሚል ጥያቄን በጥያቄ የሚመልስ ምክር አይሉት ማባላት ምላሽ እንደሰጡ በቅርበት የሚያውቋቸው ግለሰቦች ይናገራሉ፡፡ እንግዲህ ይህ አባባላቸው “ሌባ ተይዞ ዱላ አይጠየቅም” የሚለውን ይትብሃል የሚያመላክት ብቻ ሳይሆን፣ ‘መሳሪያ የታጠቃችሁት ለጌጥ ነው እንዴ?’ በሚል አንድምታ በደንብ ጨፍጭፏቸው የሚል የሚዘገንን ምክርንም ያዘለ ነው፡፡

እርግጥ ይህ የኘሮፌሰሩ በገዛ ወገን ላይ የተሰጠ ጭካኔ የተሞላበት “ግደልና አሳየኝ” ምክር ሰቅጣጭ ነው፡፡ ገዳይን ከመኮነን ይልቅ የተኩሰህ ግደል አማካሪነት ምንኛ ሰብአዊነት የጐደለው ተግባር እንደሆነም ልብ ማለት ይገባል፡፡ እኚህ ኘሮፌሰር በሚገርም ሁኔታ ዛሬ ላይ ሆነውም ይህን መሰሉ ጥያቄ እንዲቀርብላቸው ሳይመኙ የሚቀሩ አይመስለኝም፡፡ ለምን ቢባል፣ በሰው በላው የደርግ ስርዓት ወቅት ደም እያሸተቱ የኖሩ ግለሰብ ከመሆናቸውም በላይ፣ አሁንም በመግቢያቸው ላይ በገፀ-ባህሪነት ያስተዋወቁን የደቡብ አፍሪካው ግለሰብ “...ይህንን ሁሉ መንገድና ህንፃ በአንድ ጊዜ ለማሰራት ገንዘቡን ከየት ነው የምታመጡት?...” ብሎ ጠየቀኝ ላሉት ጉዳይ፣ ምላሻቸው ህዝቡ በኮንደሚኒየም ቤት ግንባታ ተጠቃሚ እንዳይሆን የመልማትና የማደግ ወኔውን ለመስለብ ጥረት

እያደረጉ ነው፡፡ በእኔ እምነት አንድ ህዝብ ሁሌም በድህነት አረንቋ ውስጥ እየዳከረ እንዲኖር ከልቡ የሚመኝ ምሁር ነኝ ባይ እኩይ መካሪ የህብረተሰቡ ቁስል ነው—በውሸት በመቀላመድ ውስጥ ውስጡን እያመረቀዘ ህዝቡን ገዝግዞ ለመጣል የሚሞር። ይህ ደግሞ በተዘዋዋሪ መንገድ ማህበረሰቡን የመግደል ተግባር ነው—እንደ ደርግ ጊዜው በጠብ-መንጃ "ግደልና አሳየኝ" ዓይነት ምክር ባይሆንም። እናም የእርሳቸውን ቋንቋ ቃል በቃል ልዋስና፤ ለእኔ ሰውዬው ራሳቸው ረብ ያለው ነገር ለህብረተሰቡ ሳይከውኑ ሀገራችን ውስጥ ተጎልተው ህዝቡ ፊቅ ያለ ህይወት እንዳይኖር የሚመኙ "የሥላሴዎች እርግማን" ናቸው። ለዚያውም በሶስት ስርዓቶች።

ታዲያ ነብር ዥንጉርጉርነቱን እንደማይለውጥ ሁሉ፤ ፕሮፌሰሩም ይህን ማንነታቸውን ዛሬም የተው አይመስሉም። እንዲያውም በሶስቱም ስርዓት ያካበቱትን ፀረ-ህዝብ ባህሪያቸውን በማዳበራቸው ምክንያት ይኸው ተውሳካቸው ብሶባቸዋል ማለት ይቻላል። ለዚህ ደግሞ አስረጅ ፍለጋ ሩቅ መሄድ አያስፈልግም። በፅሑፋቸው ላይ መንግስት በፈጠረለት ምቹ ልማታዊ ሁኔታ ከገቢው ቆጥቦ የቤት ባለቤት ለመሆን ሌት ተቀን የሚሰራውን የሀገራችንን ታታሪ ህዝብ የሰደቡበትን አባባል መጥቀስ ይቻላልና። አዎ! ሰውዬው ህዝቡንና የቁጠባ ባህሉን "…ድሃዎች ለማይኖሩበት ቤት ኪራይ አስቀድመው ይከፍላሉ! ማንም አላስገደዳቸውም፤ ያስገደዳቸው ደካማነታቸውና መናጢ ድህነታቸው ነው፤ መስገብገባቸው ነው።" በማለት ዘልፈውታል፤ አንጓጠውታል።

እርግጥ ህዝብ እንደ ህዝብ አይሰደብም፤ አይንጓጠጥም። ለዘያውም የልማት አስፈላጊነትን ተረድቶ ራሱን ለመቀየር ደፋ ቀና የሚል ህዝብ ይከበራል፣ ይታፈራል፣ አይዞህ ይባላል እንጂ፤ በማንነቱና ለማደግ ባለው ቀናዒ ፍላጎቱ "መናጢ ድሃ፣ ስግብግብ…ምንትስ" እየተባለ የስድብ ናዳ ሊወርድበት ባልተገባ ነበር።…ግና ፕሮፌሰሩ ምን አለባቸው? እርሳቸው በሶስት ሰርዓቶች ኪራይ በመሰብሰብ ባካበቱት ገንዘብ ቪላ ውስጥ እየኖሩ በድሃው ህዝብ የኮንደሚኒየም ቤት ባለቤትነት ፍላጎት ላይ ቢሳለቁ ምን ገዷቸው?—ምንም። "ዘመናይና እብድ እንዳሻቸው ይናገራሉ" እንደሚባለው ሰውዬው በድሃው የልማት ቁጭት ቁስል ላይ እንጨት መስደዳቸው የሚገርም አይደለም። ዳሩ ግን ህዝቡ ፕሮፌሰሩ ያማከሯቸው በነበሩት ያለፉት ስርዓቶች ቆርቁዞ ዛሬ ላይ አንገቱን ቀና ለማድረግ እየሞከረ በመሆኑ፤ የሰውዬውን ንቀት አዘል ስድብ በትዝብት ከመመልከት ውጪ አደህይቶ የማየት የዓላማቸው ሰለባ ሊሆን እንደማይችል አሳምሮ ያውቀዋል። ለምን ቢባል ፕሮፌሰር መስፍን ዕድሜ ልካቸውን ከአንዱ ስርዓት ወደ ሌላኛው እየተገለባበጡ በመምጣት ፀረ-ህዝብ ድቤ በመምታት የሚታወቁ መሆናቸው ከማንም የተሰወረ ጉዳይ ባለመሆኑ ነው—ተግባራቸው "ግመል ሰርቆ አጎንብሶ" እንዲሉት ያህል የአደባባይ ምስጢር ነውና።

ኧረ ለመሆኑ ፕሮፌሰሩ እንደሚሉት ድሃው ህዝብ ለኮንደሚኒየም ቤት ግንባታ የሚቆጥበው ገንዘብ ላልኖረበት ቤት አስቀድሞ ኪራይ እንደ መክፈል ይቆጠራልን?–አዎ በእርሳቸው እምነት ነገ የቤት ባለቤት እሆናለሁ ብሎ የሚያልመው ህዝብ ለኮንደምንየም ቤት ለአምስት ዓመታት ዛሬ ላይ የሚያጠራቅመው ብር ከአምስት ዓመታት በኋላ ለሚኖርበት ቤት ኪራይ በመክፈል በመንግስት እየተበዘበዘ ነው።...እውነታው ግን ሰውዬው እንደቀላመዱት አይደለም። እርግጥ ቁጠባ በአንድ ሀገር ምጣኔ-ሀብታዊ እመርታ ውስጥ ያለውን አሉታዊ ድርሻ ለፕሮፌሰሩ ማስረዳት የሚያሳፍር ነው። ቢያንስ እነ ቻይና ለዛሬው ዕድገታቸው የበቁት እያንዳንዱ ዜጋ ከሚያገኘው ገቢ በመቆጠቡ መሆኑን ሊያውቁት ስለሚችሉ ነው። እናም ማንም ሰው ከገቢው የሚቆጥበው ነገ ለሚያከናውነው ጉዳይ እንጂ አሁን ላይ ለመከወን ለሚፈልገው ተግባር አለመሆኑን ከጥላቻ አሉባልታ ወጥቶ መገንዘብ አስፈላጊ ይመስለኛል።

እንበልና አንድ በ10/90 የቤቶች ግንባታ ፕሮግራም ለባለ ሁለት መኝታ በወር 274 ብር ለመቆጠብ የተመዘገበ፣ ነገር ግን በግለሰብ ቤት ተከራይቶ የሚኖር ግለሰብ አለ። ይህ ግለሰብ በዚሁ ተከራይነቱ ቢቀጥል የዛሬ አምስት ዓመት ያው ተራይ መሆኑን ተማርኩ ባይ ፕሮፌሰሩ የሚክዱት አይመስለኝም። ከአምስት ዓመት ቆይታ በኋላም ቢሆን ከተከራይነቱ በስተቀር የራሱ ቤት ሊኖረው አይችልም። ይሁንና ግለሰቡ ለቀጣዮቹ አምስት ዓመታት በተመዘገበበት የ10/90 ፕሮግራም ከሚያገኘው ገቢ ቢያጠራቅም የቤት ባለቤት ይሆናል እንጂ ለማይኖርበት ቤት እንዴት አስቀድሞ ኪራይ እንደሚከፍል ከፕሮፌሰሩ የጥላቻ ዲስኩር በስተቀር ለማንም ግልፅ አይደለም። እርግጥ ፕሮፌሰሩ ሁሉንም ነገር አውቃለሁ ባይ ስለሆኑ እንጂ እንዲህ ያለው የሂሳብ ጉዳይ ለታሪክ ሰው አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። በዚያ ላይ ደግሞ እርጅና ሲጨመርበት ስሌታቸው የተዘበራረቀ ሊሆን እንደሚችል ግልፅ ነው።

እርግጥ ፕሮፌሰሩ እንዲህ ዓይነቱን ጉዳይ መስማት ባይፈልጉም፤ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ግን የመኖሪያ ቤት ፍላጎት በአንድ ሀገር ውስጥ ከሚገኘው የሃብት መጠን ውስጥ 50 በመቶውን የሚሸፍን ነው፡፡ ዜጎችን የቤት ባለቤት ማድረግ ማለት ይህንን የሀገር ሃብት በአብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል በተለይ በአነስተኛ ገቢ በሚተዳደሩ አካላት መካከል እንዲሰራጭ የሚያደርግ በመሆኑ ይበልጥ ፍትሃዊነትን ለማረጋገጥ የሚኖረው ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡ ታዲያ ከዚህ አኳያ ልማታዊው መንግስት በነደፈው የከተማ ቤቶች ፖሊሲና ስትራቴጂ በግልፅ እንዳስቀመጠው ይህን ለማስፈፀም በዋነኛነት ሁለት መንገዶችን ይህን ይከተላል፡፡

አንደኛው በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ላሉና በከተሞች ውስጥ በሚታየው የቤት ችግር ግንባር ቀደም ተጠቂ የሆኑ ነዋሪዎች ተጠቃሚ የሚሆኑበትንና በረጅም ጊዜ ሂደት ራሳቸውን የቻሉና የቤት ባለቤት ስለሚያደርጋቸው ፍትሃዊ የሆነ የሃብት ክፍፍል ሥርዓት እንዲፈጠር ማድረግ ነው፡፡

ሁለተኛው ደግሞ መካከለኛ ገቢ ያላቸው የከተማ ነዋሪዎችን ፍላጎትና የቁጠባ አቅም ላይ ተመስርቶ በሚሰጥ የባንክ ብድር ቤቶችን በመገንባት ዜጎችን የቤት ባለቤት ማድረግ ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል ሥርዓቱን ማጠናከር ነው፡፡ ፕሮፌሰሩ ግን በፊውዳላዊ አስተሳሰብ ጎልምሰው ያረጁ በመሆናቸው 'የራሴን ድርሻ እስከያዝኩ ድረስ ስለሌላው ፍትሐዊ የሃብት ክፍፍል ምን ያገባኛል? በሚል አደናቋሪ እሳቤ በመኳዝ ዛሬም ይህን ዕውነታ ለመስማት አይፈልጉም። ለዚህም ነው የማያውቁበትን የሂሳብ ስሌት በመቀመር ድሃውን ህዝብ እየተሳደቡ ወኔውን ለመስለብ እየሞከሩ ያሉት።

የዚህን ፅሑፍ አቅራቢ እጅግ ያስገረመኝ ሌላኛው ጉዳይ፣ መንግስት በቤቶች ግንባታ ፕሮግራሙ በድኅማ በመስራት ለህዝቡ የሚሰጠው ቤት ለጭፍን ተሚጋቹ አላዋቂ ፕሮፌሰር እንዴት "ብዝበዛ" ሊሆን እንደቻለ ነው። ለነገሩ ሁሉንም ነገር በደፈናው ለሚቃወም ሰው ዳቦም ድንጋይ ሊሆን ይችላል። ሆኖም ይህ የሰውዬው አስገራሚ መላ-ምት ሁለት ነገሮችን ሸምጥጦ የሚክድ በመሆኑ ፈፅሞ ተቀባይነት የለውም። አንድም ፀረ-ህዝብነት ያደቆናቸው እኚህ ግለሰብ የሚሰድቡትንና በድህነቱ የሚያዋርዱትን ህዝብ ወክለው የመከራከር ሞራል የሌላቸው ሲሆን፣ ሁለትም ሰውዬው ህዝቡ በማያሻማ ሁኔታ የሚያውቀውን የመንግስትን የድኅማ አሰራር በስብቀት ለመደፍጠጥ መሞከራቸው ነው። እስቲ ሁለቱንም ጉዳዮች በአርምሞም ቢሆን እንመልከታቸው።...

በቅድሚያ ኘሮፌሰሩ በሌለ ነባራዊ ሁኔታ በፍፁም የጥላቻ ስሜት የመንግስትን ህዝባዊነት ለማጣጣል እየሞከሩ ህዝቡ እንዳይጠቀም አዋራ ለማስነሳት የፈለጉበት ዋነኛ ምክንያት ለእኔም ሆነ ለዚህ ፅሑፍ አንባቢ ግልፅ ይመስለኛል፡፡ እርሱም በሀገራችን ውስጥ ያልነበረ፣ ነገር ግን ልማታዊው መንግስት በሀገራችን ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ዜጎችን የዘመናዊ ቤት ባለቤት ለማድረግ እያደረገ ያለው ጥረት በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነትና ድጋፍ ያለው በመሆኑ ይኸው ሁኔታ የሚያስደነግጣቸው መሆኑ ነው፡፡ እርግጥም ከራሱ ጩኸት በስተቀር የህዝቡን መሰረታዊ ችግሮች ከቁብ የማይቆጥርና በድሃው ስቃይ የሚሳለቅ ግለሰብም ይሁን ቡድን የቀበሮ ባህታዊ ሆኖ ለማህበረሰቡ ሊያስብ የሚችልበት ሞራል የለውም። ይህን ላድርግ ቢል እንኳን ውስጣዊ ማንነቱ ሳያውቀው እያፈተለከ ያሳጣዋል–ልክ ፕሮፌሰር መስፍን ለይስሙላ ለህዝቡ ያሰቡ መስለው በአላዋቂነት የሂሳብ ስሌት ሰርተው ሲያበቁ፣ መልሰው ህዝቡን እንደሰደቡት ዓይነት ማለት ነው።

በሌላ በኩልም ፕሮፌሰሩ እንደቀላመዱት የመንግስት ዓላማ ህዝቡን መበዝበዝ አይደለም–በድኅማ የቤት ባለቤት በማድረግ የመኖሪያ ቤት ችግሩን መፍታት እንጂ። ለዚህም መንግስት በከተማ ቤቶች ፖሊሲውና ስትራቴጂው ላይ ያሰፈረውን የቤቶቹን ግንባታን አስፈላጊነት እንዲሁም በምን ዓይነት የፋይናንስ ምንጭ ቤቶቹ እንደሚገነቡ መመልከት ይቻላል–በተቃውሞ አታሞ ያልተደፈነ ጆሮ ካለ ማለቴ ነው። እርግጥ ለሀገራችን የከተማ ነዋሪ የቤት ችግር መንስኤዎቹ ሁለት ናቸው።

አንደኛውና ዋነኛው ችግር የመኖሪያ ቤት እጥረት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ያረጁና የተፋፈጉ የከተማ ሰፈሮች መስፋፋት ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ በሚገኙ ከፍተኛና መካከለኛ ከተሞች እና በአዲስ አበባ ይኖራል ተብሎ የሚገመተው የቤት እጥረት በጣም ከፍኛ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በከተሞች ያለው የቤት አቅርቦትና ፍላጎት ያልተጣጣመ መሆኑንና ከፍተኛ የሆነ የመኖሪያ ቤት እጥረት መኖሩን የሚያመላክት ነው፡፡ እናም ይህ የመኖሪያ ቤት ፍላጎትና አቅርቦት ያለመመጣጠን አብዛኛውን የኀብረተሰብ ክፍል ተገቢ ላልሆነ ወጪና መንገላታት በመዳረግ ለተወሳሰበ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኀበራዊና ሥነ-ልቦናዊ ችግሮች እያጋለጠው ይገኛል–ምንም እንኳን ፕሮፌሰሩ ይህን ሃቅ የማያውቁት ቢሆኑም። ከዚህ በተጨማሪም ምርታማነትን በመቀነስና በዚህም መነሻነት በከተሞቹ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ በማሳደር በከተሞች ልማት ላይ የበኩሉን ጫና ፈጥሯል፡ ፡ ይህም ነዋሪዎች በተለያዩ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ በየደረጃው የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዳያበረክቱ ቀላል የማይባል ማነቆ ሲሆን ይስተዋላል፡፡

ከዘህ ጎን ለጎንም በከተሞች ለሚገኘው የቤት እጥረት መገለጫነት ከሚጠቀሱት ምልክቶች ውስጥ ተጠቃሽ ምክንያት በተጨናነቀ ሁኔታ የሚኖሩ ቤተሰቦች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱ ነው፡፡ ይህም በአንድ ቤት በሚኖሩ የቤተሰብ ብዛት፣ በአንድ ቤት ውስጥ ባሉ ክፍሎች እና በደባልነት በሚኖሩ አባወራዎች ቁጥር ሊገለፅ ይችላል፡፡ ደባልነትን በተመለከተ በ1986 እና በ1999 ዓተ ምህረቶች የተደረጉት የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ መረጃ ውጤት እንደሚያሳየው፤ በርካታ የከተማ አባወራዎች በቤት እጦት ምክንያት ሳይፈልጉ በደባልነት ይኖራሉ፡፡ በሌላ በኩል የ1999 ዓ.ም የቆጠራ ውጤት እንደሚያሳየው በከተሞች ከሚገኙት ቤቶች ውስጥ ወደ 50 በመቶ የሚሆኑት ባለ አንድ ክፍል ቤቶች ናቸው፡፡ ክፍሎቹ በጣም ጠባብ በመሆናቸው አንዳንዴ እስከ 11 የሚደርሰውን የቤተሰብ ብዛት የሚያኖሩ ናቸው፡፡ እናም አብዛኛው በተለይ በከተሞች ማዕከላዊ ክፍል የሚገኘው ነዋሪ ደረጃቸው በጣም ዝቅተኛ በሆኑ ቤቶች በተጨናነቀ ሁኔታ እንደሚኖር መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

ወደ ሁለተኛው ችግር ስናቀና ደግሞ የሀገራችን ከተሞች በአብዛኛዎቹ የማዕከላዊ የከተማ ክፍሎች ከፕላን ውጭ ነዋሪዎች በመከማቸታቸው በእርጅና ምክንያት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አገልግሎቶች የተጓደሉ በመሆኑ ለሰው ልጅ መኖሪያነት ምቹ ያልሆኑ የከተማ አካባቢዎች ሆነዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በእነዚህ አካባቢዎች በመንግስትም ሆነ በግል ይዞታ ሥር የሚገኙ መኖሪያ ቤቶች ሁኔታ ሲታይ ደረጃቸውን ያልጠበቁ፣ ከተገነቡ ረጅም ጊዜ የሆናቸውና የተገነቡበት ቁሳቁስ ለማደስ የማያስችላቸው ዓይነት ናቸው፡፡ በእርጅናና ተገቢው ጥገና ባለማግኘታቸው

ምክንያት በአብዛኛዎቹ ከተሞች የሚገኙ ቤቶች በተለይም በከተማ አስተዳደር ሥር የሚገኙት ወደ መፍረስ ደረጃ የተቃረቡ በመሆናቸው ፈርሰው አካባቢው ዳግም መልማት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

እንግዲህ ፕሮፌሰሩና ጀሌዎቻቸው የሚሰሙ ከሆነ እነዚህን ሁለት ችግሮች በቀዳሚነት ለመፍታት ነው– መንግስት የኮንደሚኒየም ቤቶች ግንባታ ላይ እየተረባረበ የሚገኘው። እነርሱ ከራሳቸው ኪራይ ሰብሳቢ ባህሪ በመነሳት እንደሚያስቡት የህዝቡን ገንዘብ በመሰብሰብ ያልኖረበትን ኪራይ በቅድሚያ በማስከፈል ለመበዝበዝ አይደለም። ለነገሩ አንድ መንግስት ለሚሰራው ቤት ድጎማ እያደረገና ብድርን በረጅም ጊዜ ለህዝቡ እያመቻቸ እንዴት የገዛ ህዝቡን እንደሚበዘብዝ ከፕሮፌሰሩ ሾላ በድፍን የሆነ የተቃውሞ ሽውራራ ዕይታ በስተቀር ለማንም ግልፅ የሚሆን አይመስለኝም። ኧረ ለሽውራራ ዕይታውም ቢሆን ግልፅ የሚሆን አይደለም–የመጃጃት ውጤት ካልሆነ በስተቀር። ታዲያ እዚህ ላይ መንግስት በየትኛው የፋይናንስ ምንጭ ህዝቡን የቤት ባለቤት ለማደረግ ቆርጦ እንደተነሳ ፕሮፌሰሩን እየመረራቸውም ቢሆን ዕውነታውን ሊጋቱት ይገባል ባይ ነኝ።

እንደሚታወቀው በመንግሥት አስተባባሪነት ለሚገነቡ ቤቶች ተጠቃሚ ከሚያደርጉት የህብረተሰብ ክፍል የገቢ አቅም አኳያ ምጣኔው ወደፊት በሂደት የሚሻሻል ሆኖ፤ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ከሚወሰነው የማስተላለፊያ ዋጋ 10 በመቶ፣ በተቀናጀ የቤት ልማት ፕሮግራም ተጠቃሚዎች ከማስተላለፊያ ዋጋው 20 በመቶ እንደ ቅደም ተከተላቸው በ2 እና በ5 ዓመት እንዲቆጥቡ የሚደረግ ነው፡፡ የማስተላለፊያ ዋጋው 90 በመቶ እና 80 በመቶ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ወይም ወኪሎች የረጅም ጊዜ ብድር እንዲመቻችላቸው አቅጣጫ ተቀምጦ በመፈፀም ላይ ያለ ነው፡፡ የ40/60 የቁጠባ ቤቶች ልማት ተጠቃሚዎችም ቢሆኑ ምጣኔው ወደፊት በሂደት የሚሻሻል ሆኖ፤ ከሚመርጡት የቤት ዓይነት ዋጋ 40 በመቶ እስከ 5 ዓመት በሚደርስ ጊዜ እንዲቆጥቡ ተደርጐ ቀሪው 60 በመቶ ድጎማ ባለው አነስተኛ የወለድ ምጣኔ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የረጅም ጊዜ ብድር እንዲያገኙ ተወስኖ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡…ታዲያ የፕሮፌሰሩ "ብዝበዛ" የተሰኘው የቅጥፈት ትርጓሜ ምኑ ጋ ነው ያለው?– እናንተዬ በየትኛው ተቃውሞአዊ መዝገበ ቃላት ነው ድጎማና የረጅም ጊዜ ብድር "መበዝበዝ" ተብሎ ጥቅል ትርጓሜ የተሰጣቸው?– ምናልባት "አንድነት" በተሰኘውና የከሰሩ ጠንቋዩች ስብስብ የሆነው የሰውዬው የቀድሞ የፖለቲካ ቡድን ምስጢራዊ ብያኔ ይሆን እንዴ?–ማን ያውቃል?!...ቂ.ቂ.ቂ….

ምንም እንኳን ፕሮፌሰሩ የኮንደሚኒየም ቤት ግንባታን በተመለከተ በፅሑፋቸው ላይ ያነሷቸው አራት ጥያቄዎች እንኳንስ "ከእኔ ወዲያ ላሳር" ከሚል "አዋቂ ነኝ" ባይ ቀርቶ ከተራው ዜጋም የማይጠበቅ ቢሆንም፤ ጭፍኑ ግለሰብ የተቃውሞዬ ማጀቢያ ይሆኑኛል በሚል ያቀረቧቸው እንደ እርሳቸው ያረጀ የፕሮፖጋንዳ ዘዴ በመሆኑ ጥቂት በጉዳዩ ዙሪያ ማለት ተገቢ ይመስለኛል።

በግለሰቡ ፅሑፍ ላይ የተነሱት አስቂኝ ጥያቄዎች ጠቅለል ተደርገው ሲታዩ "...**አንደኛ** ስራው መቼ ተጀምሮ መቼ ያልቃል?፣ **ሁለተኛ** ኮንደሚኒየሙ ስንት ክረምትና ስንት በጋ የሚችል ይሆናል?፣ **ሶስተኛ** ኮንደሚኒየሙ 'ሊፍት' አለው ወይ? ለአረጋውያንስ ታስቧልን?፣ **አራተኛ** ስለ ጤና ምን ታስቧል?" የሚሉ ናቸው።

ታዲያ ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እነዚህን አስገራሚና አስቂኝ እንዲሁም የጥላቻና የማጥላላት ማሚያ ጥያቄዎችን ሲመለከት፤ መልሶ ራሱን 'የተማሩትና የተመራመሩት እኚህ ግለሰብ ስለ ኮንደሚኒየም ቤቶች ግንባታ ምንም አያውቁም እንዴ?' የሚል ጥያቄ ሊጠይቅ ይችላል። እርግጥ ጥያቄው ትክክል ነው። ሰውዬው እየዘላበዱ ያሉት ስለማያውቁት ነገር ነው። ለነገሩ እርሳቸው ስለ ህዝቡ ተቆርቋሪ መስለው ለይስሙላ ጨለማ ውስጥ በሚድኸው ወልጋዳ ብዕራቸው ደሰኮሩ እንጂ፣ ህዝቡ ለመኖር የሚፈልገውን የአኗኗር ዘይቤ እንኳን በቅጡ የሚያውቁ አይደሉም። ለዚህም ነው በጥላቻ ፈረሳቸው ላይ ያለ ሃፍረት ተቀምጠው በመያውቁት ነገር አንዴ መንግስትን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ህዝቡ ውስጥ ሳይኖሩና ፍላጎቱን ሳያውቁ ስለ ህዝቡ በመናገር፣ በል ሲላቸውም በመሳደብ ራሳቸው ተደናግረው ሌላውንም ለማደናገር የሚጥሩት። እናንተዬ ማን ነበር "በህዝቡ ውስጥ የሌለ የትም የለም" ያለው?–መቼም ስለ ሚከራከሩለት የኮንደሚኒየም ቤት ግንባታ የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል ዕውቀት የሌላቸው "ሊቁ" ፕሮፌሰር የሚሆኑ አይመስለኝም።

ያም ሆነ ይህ ግን የሰውዬውን አራት ጥያቄዎች በሁለት ከፍሎ መመልከት ይቻላል–የቤቶቹ ግንባታ አፈፃፀም እና ህዝቡ ቤቱን ከተረከበ በኋላ ስለሚኖረው ማህበራዊ ህይወት በሚሉ ጉዳዮች።

እንደሚታወቀው የየትኛውም ሀገር መንግስት የኮንደሚኒየም ቤቶች ልማትን ሲሰራ በሚገባ አስቦበትና በጥናት ተደግፎ ነው። ከዚህ አኳያ የኢፌዴሪ ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መንግስት ልማቱን ለማካሄድ ሲያስብ በቂ ጥናት አድርጎ እንጂ እንደ እነ ፕሮፌሰሩ ተቃውሞ "የእነ ቶሎ ቶሎ ቤት..." ዓይነት ስራን ለመከወን አይደለም። በዚህ መሰረትም  መኖሪያ ቤት የሌላቸው አነስተኛና መካከለኛ እንዲሁም ከፍ ያለ ገቢ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የህዝብ ብዛትን መሠረት ባደረገ የከተሞች ደረጃ የተለያዩ ወጪና መሬት ቆጣቢ የሆኑ ስታንዳርድ ዲዛይኖች በማዘጋጀት ወጪ ቆጣቢ ቤቶች በልዩ ሁኔታ ከከተማው ፕላን ጋር በማጣጣም የሚከናወን ተግባር ገቢራዊ እያደረገ ነው። በመሆኑም ለግንባታው የሚቀርቡት ግብዓቶችም ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ጥብቅ ቁጥጥር ያደርጋል። ደረጃውን የጠበቀ ማንኛውም ዓይነት ግንባታ ደግሞ ዕድሜው ረጅም መሆኑ አያጠያይቅም። ግንባታው ከአዛውንቶች ባሻገር አካል ጉዳተኞችንም ታሳቢ ያደረገ ነው። እንደ ግንባታው ርዝመትም የሚገነቡት ቤቶች ሊፍት ወይም አሳንሰር ሊኖራቸው ይችላል።

በቤቱ ግንባታ ሳቢያ ሊከሰት የሚችለው ማህበራዊ ሁኔታ፣ በተለይም የህዝቡን ጤና ከመጠበቅና በሽታን አስቀድሞ ከመከላከል አንፃር በመንግስት በኩል አስቀድሞ የታሰበበት ጉዳይ

መሆኑን አላዋቂው ፕሮፌሰር ቢረዱት በጄ ነው። ምክንያቱም ይህ ተግባር የኮንደሚኒየም ቤቶች ግንባታ ሀገራችን የምትታወቅበትን የአረንጓዴ ልማት አቅጣጫን በመደገፍ ረገድ ያለውን ፋይዳ ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ስለሆነ ነው።

እርግጥም ከመኖሪያ ቤቶች ልማት ጋር በተያያዘ በአረንጓዴው ልማት ስትራቴጂ የተቀመጡትን አንኳር ጉዳዮች በተሟላ መልኩ መተግበር ፋይዳው ከፍተኛ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ለከተማ ነዋሪዎች ምቹ የመኖሪያ፣ የስራና አዕምሮ ማሳረፊያ ቦታ ከመፍጠር፣ የከተማውን አረንጓዴነት ከመጠበቅና ለከተሞች ውብ ገፅታ ከማላበስ አኳያ፤ ዜጎች በግልና በጋራ በግቢያቸው ውስጥና በአካባቢው እንዲሁም በመልሶ ማልማት ወቅት የሚፈጠሩ ክፍት ቦታዎችን በዕፅዋት የሚያለሙበትን አሠራር በመዘርጋት መተግበር የመኖሪያ አካባቢዎችን ለኑሮ ምቹ ከማድረግ አኳያ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በሽታን ለመቆጣጠርና ከተከሰተም አስቀድሞ ለመከላከል ጉልህ ድርሻ አለው።

ከዚህ ባሻገርም በመኖሪያ መንደሮች የከተማ ፓርኮች ልማት በማካሄድ ለነዋሪዎቻቸው የመዝናኛ አገልግሎት በመስጠት፣ የከተማውን ተፈጥሮአዊ ገፅታ በመጠበቅ፣ የከተማውን ውበትና አካባቢያዊ ጥራት በማጎልበት፣ የማህበረሰቡን ግንኙነት በማጠናከር በተለይም በከተማ ለሚኖሩ ገቢያቸው ዝቅተኛ ለሆኑና ብሔራዊ ፓርኮችን ለመጎብኘት ዕድል ለማይኖራቸው ጥሩ አማራጮች በመሆን እንደሚያገለግሉ ፕሮፌሰሩ ሊረዱት ይገባል፡፡

ታዲያ ስለ ኮንደምንየም ቤት ግንባታ ያለው ዕውነታ ይህ ከሆነና ቀደም ሲል በጠቀስኳቸው ጉዳዩች ከተግባባን ዘንዳ፤ 'የፕሮፌሰሩ የቅጥፈት ዲስኩርና ማምታታት ከየት የመጡ ናቸው?' የሚል ጥያቄን ማንሳት ግድ ይለናል። ምላሹ ግን አጭር ነው—የተቃውሞው ጎራ የራሱ ፖሊሲና ስትራቴጂ ሳይኖረው በመንግስት የልማት አጀንዳዎች ላይ በመንጠላጠል አዎንታዊ ስራዎችን የማጣጣል ምንም የማይፈይድ የመቀላመድ አባዜ። ለልማቱ አንድ ድንጋይ ሳያቀብሉ የሚሰራውን ህዝብ በባዶ የወረቀት ላይ ጩኸት የማወናበድ የሞኞች ፈሊጥ ቢባልም ያስኬዳል። ጩኸቱ ግን የቁራ ነው—ታታሪው የሀገራችን ህዝብ የሚሰራን እንጂ ዕድሜ ያላስተማረውን የጨለማ ዘማሪ የፈጠራና የጥላቻ እንጉርጉሮን የሚያዳምጥበት ጊዜ የለውምና። በራሳቸው ተድላና ፍሰሐ ውስጥ በእብሪት ብቻቸውን እየዋኙ የሚሰድቡትንና ከድህነት ለመውጣት የሚያደርገውን ጥረት የሚያንጓጥጡትን "የስላሴ እርግማኖችን" ዞር ብሎ አያያቸውምና። ያም ሆነ ይህ ግን እኔ የዚህ ፅሑፍ አቅራቢ ሰውዬው ቢሰሙም፣ ባይሰሙም እንዲህ በማለት ፅሑፌን ለመቋጨት ወደድኩ። ፕሮፌሰር ሆይ፣ ምናለበት በዚህ ዕድሜዎ ባይቀላምዱ?!። አበቃሁ።